በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

ፕሬስ መግለጫ PRESSRELASE

# ሚዲያ የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ትብብር የማሻሻል እና ችግሮችን የማሳየት ኃላፊነት አለበት

ሚዲያ ኢትዮጵያ ከሌሎች አካላት ጋር የምታደርገውን የዲፕሎማሲ ትብብርን ለማሻሻል ችግሮችን ለማሳየት



የሚያስችል ብቃት ሊኖረው እንደሚገባ ተገለጸ፡፡

የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ወ/ሮ ሂሩት ዘመነ ለሁለት ቀናት ያክል በተሰጠው የጋዜጠኞች ስልጠና የመዝጊያ ስነ-ስርዓት ላይ ባደረጉት ንግግር ሚዲያ ለአንድ አገር እድገት በተለይም ለዲፕሎማሲ ስራ ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በመረጃ የታጠቀ ህብረተሰብ ከመፍጠር አንጻር የሚዲያው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን በመጥቀስ ሚዲያ በዲፕሎማሲው ዓለም ተጽዕኖ በመፍጠር የአገርን ጥቅም በማስጠበቅ በኩል ያለው ፋይዳ ከፍ ያለ መሆኑን ክብርት ሚኒስትር ዴኤታዋ ተናግረዋል፡፡

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson, YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00 ✉393 Addis Ababa,Ethiopia

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ህብረተሰቡን የመረጃ ተደራሽነት ለማድረግ ከሚዲያ ጋር ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ ወ/ሮ ሂሩት በስልጠናው ዝግጅት ተሳትፎ ያደረጉትን የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ቃል አቀባይ ጽ/ቤትን፣ የውጭ ግንኙነት ማሰልጠኛ ተቋምን እንዲሁም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመስግነዋል፡፡

የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አቶ መለስ በበኩላቸው ለሰልጣኞቹ ባደረጉት ማብራሪያ የአገራችን ሚዲያዎች ጋር ለጋራ አገራችን ተግተን ልንሰራ ይገባል ብለዋል፡፡ ሚዲያ የአገርን ገጽታ ለመገንባት አይነተኛ መሳሪያ መሆኑን በመጥቀስ በእውቀት ላይ በመመስረት ነባራዊ ሁኔታን በመተንተን ለአገር ልማት፣ ሰላምና ደህንነት መስራት ከአገራችን ሚዲያ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነት ሙሁር ዶ/ር ቶን ቪን ለሰልጣኞቹ ባደረጉት ገለጻ ሚዲያ መንግስትን ከመንግስት፣ መንግስትን ከህብረተሰብ እንዲሁም ህብረተሰብን ከህብረተሰብ የሚያገናኝ ድልድይ ነው ፡፡ የቃል አቀባይ ጽ/ቤት የሚኒስቴር መ/ቤቱ አይንና ጆሮ መሆን ብቻ ሳይሆን ለህብረተሰቡ በቂ መረጃ የመስጠት ኃላፊነት አለበት ብለዋል፡፡

ዶ/ር ቶን አያይዘውም ሚዲያ ግልጽነት በተሞላበት መንገድ መረጃዎችን በማሰራጨት ለመንግስትም ይሁን ለህብረተሰቡ ጠቃሚ መረጃዎችን የሚጠቁም ለአገር ፖሊሲ ቀረጻ ትልቅ ሚና የሚጫወት ነው ብለዋል፡፡

ስልጠናውን የወሰዱት የሚዲያ ባለሙያዎቹ በስልጠናው ዘርፈ ብዙ እውቀት መገብየታቸውን በመግለጽ ተመሳሳይ ስልጠናዎች ለወደፊቱም እንዲዘጋጁና በወቅታዊ አለም ዓቀፋዊ ጉዳዮች ላይ በቂ ትጥቅ እንዲኖረን እንፈልጋለን ብለዋል፡፡

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**ሰኔ 5 ቀን 2010 ዓ.ም.**